
የብልጽግና ፓርቲ

# የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) መተዳደሪያ ደንብ

## በብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ)

ግንቦት 2015




መተዳደሪያ ደንቡ በ5 ምዕራፎችና በ42 አንቀፆች የተከፋፈለ ነው

# መግቢያ

- ሀገራችንን ወደሚቀጥለው ምእራፍ ለማሻገር አዲስ ራእይና አዲስ ትርክት እንደሚያስፈልግ በማመን፤
- የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፤ የግለሰብና የቡድን መብቶች በሚዛኑ የሚከበሩባት፤
- ዜጎች ከድህነት ተላቀው በብልጽግና የሚኖሩባት፤ ጠንካራና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታይባት፤
- የበለፀገች፣ ኅብረብሔራዊ ማንነቷ የዳበረና አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ
- በመደመር አስተሳሰብና በአንድነት ቅኝት በመነሣት፣ ልናያት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የእያንዳንዳችንን ርብርብ የሚጠይቅ ይሆናል፡፡
- ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተደነገጉትን ሕጎች መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## I. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ አንድ - አጭር ርእስ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ *"የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

**አንቀጽ ሁለት - የፓርቲው መጠሪያ**

የፓርቲው መጠሪያ **"የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)"** ነው።

# አንቀጽ ሦስት - የፓርቲው ዓርማ

## የዓርማው ቀለምና አቀማመጥ


- በክብ ነጭ መደብ ውስጥ በስተግርጌ ጥቁር ለማቀፍ የተዘጋጁ ሁለት የሰው እጅ ምስሎች
- ሦስት የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሦስት ሰዎች የሚገኙበት
- ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነጥቁ ቢጫ ቀለም ያላቸው የብርሃን ፍንጣቂዎችን

**ጥቅል ትርጉም**

ኅብረ ብሔራዊነትን፣ ሀገራዊ አንድነትን፣ ብሔራዊ ኩራትን፣ ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና የብልጽግናን አስተሳሰብ የያዘ ሆኖ ከውስጥ ወደ ውጭ እየሰፋ የሚሄድ የቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትሥሥሮችን የሚያመላክት ነው

## ዝርዝር ትርጉም

**እጅ፡-**



ብልፅግና ሁሉን አቃፊና አካታች መሆኑን ቀለሙ ጥቁር የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የጥቁር ሕዝቦች የነጻነትና የድል ተምሳሌት መሆናችንን የሚወክል ነው።



**የሰዎች ምስል፡-**

- ብልፅግና ሰው ተኮር ፓርቲ መሆኑን፣ ፓርቲው ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ብልፅግና የሚታገል
- የሰዎቹ ምስል ቀለማቸው ሰማያዊ፣ ቢጫና ሮዝ መሆኑ የኢትዮጵያን ብዝኃነት እንዲያሳይና ብዝኃነታችን የውበታችንና የጠንካራ አንድነታችን ምልክት

## ጎህ፡-

- ጎህ ጨለማን ሰንጥቆ የሚወጣ ብርሃን እንደመሆኑ መጠን ብልፅግና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታና የብርሃን ዘመን ለማሸጋገር የሚታገል ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ነው።

## አንቀጽ አራት - የፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች

1. ፓርቲው ለሁሉም የሀገራችን ቋንቋዎች ሙሉ ዕውቅና ይሰጣል።
2. በፌዴራል ደረጃ የፓርቲው የሥራ ቋንቋ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት እና ክልሎች በሕገ መንግሥታቸው የሥራ ቋንቋ አድርገው ያጸደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ።
3. የፓርቲው የየደረጃው ጽ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የሥራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም ይችላሉ።

# አንቀጽ አምስት - የፓርቲው ልሳን

1. የፓርቲው ልሳን **"ብልፅግና"** ነው።
2. የፓርቲው ልሳን በፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ብዝኃ ልሳን ነው
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የሀገሪቱ እና የውጭ ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል።



## አንቀጽ ስድስት - የፓርቲው ጽሕፈት ቤት

- የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ/ፊንፊኔ ይሆናል።
- ፓርቲው ከክልል፣ ከተማ አስተዳደር እስከ ቀበሌ በተዋረድ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል
- እንደ አስፈላጊነቱ በውጭ ሀገር ጽሕፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

## አንቀጽ ሰባት - የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆች፣ ዕሴቶችና የአሠራር ሥርዓቶች

1. የፓርቲው ዓላማዎች፤

ሀ) ጠንካራ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ቅቡልነት ያለው፣ ዘላቂ ሀገረ-መንግሥትና ኅብረብሔራዊ አንድነት መገንባት፤

ለ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት፤

ሐ) ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያሰፍን ማኅበራዊ ልማትን ማረጋገጥ፤

መ) ሀገራዊ ክብርንና ጥቅምን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት ማካሄድ።

## የፓርቲው መርሆች ፤

ሀ) ሕዝባዊነት፣

ለ) ዴሞክራሲያዊነት፣

ሐ) የሕግ የበላይነት፣

መ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፣

ሠ) ተግባራዊ እውነታ፣

ረ) ሀገራዊ አንድነትና ኅብረ ብሔራዊነት።

## የፓርቲው ዕሴቶች፤

ሀ) የዜጎችና የሕዝቦች ክብር፣

ለ) ነፃነት፣

ሐ) ፍትሕ፣

መ) ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት፣

ሠ) መከባበርና መቻቻል፣

ረ) ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣

ሰ) አሳታፊነት፣

ሸ) ግልፀኝነትና ተጠያቂነት።

## የፓርቲው የአሠራር መርሆዎች፤

- ፓርቲው የሀገሪቱን እና የክልሎችን ሕገ መንግሥት እና ሌሎች ሕጎችን በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፤
- አባላት የግል ሐሳባቸውን የማራመድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲውን ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤
- ማንኛውም አባል በፓርቲ ውስጥ እኩል ድምፅና በውሳኔ ሂደቶች ውስጥ አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፤
- የፓርቲው ውሳኔ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ነው። የተሰጠው ድምፅ ለሁለት እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል፤
- የየትኛውም የፓርቲው መዋቅር ምልዐተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላለው የጉባኤው ወይም የስብሰባው 50%+1 እና ከዚያ በላይ ሲገኙ ነው፤

## አንቀጽ ስምንት - የፓርቲው ምርጫ መርህና የአሠራር ሥርዓት

- የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፕሬዝዳንት፣ የምክትል ፕሬዝዳንቶች እና የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ጸሐፊ አመራር ምርጫ ግልጽ፣ ነጻና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ በምሥጢር በሚሰጥ ድምፅ የሚመረጡ ይሆናል።

- በፓርቲው ውስጥ በኃላፊነት ቦታዎች የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋጽኦን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል።

- ማንኛውም የፓርቲ አባል የፓርቲ የምርጫ የአሠራር ሥርዓት መሠረት በሀገሪቱ በሚካሄዱ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያና የድጋሚ ምርጫዎች ፓርቲውን ወክሎ የመወዳደር መብት አለው።

# ምእራፍ ሁለት

## አባልነት

**አንቀጽ ዘጠኝ - የፓርቲው አባል ስለመሆን**

<u>መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል</u>

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በጽናት ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ የሆነ፤

ለ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለውና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለው፤

ሐ) በኅብረ ብሔራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት ላይ ጽኑ አቋም ያለውና ዋልታ-ረገጥ አመለካከትና ተግባሮችን በጽናት የሚታገል፤

መ) ዜጎችንና ሕዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም፣ ከሙስናና ብልሹ አሠራሮች ራሱን ያራቀና ሌሎችንም የሚታገል፤

## የቀጠለ…

ሠ) የፓርቲውን ዕሴቶችና ዓላማዎችን ተቀብሎ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ የሆነ፤

ረ) ወርኃዊ የአባልነት ክፍያ ለመክፈል ፍቃደኛ የሆነ፤

ሰ) እድሜ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

ሸ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

ቀ) የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብቱ በሕግ ያልተገደበ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገፈፈ፤

## አንቀጽ ዐሥር - ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ

**አንድ የፓርቲው አባል ለመሆን የወሰነ ዜጋ በሥራ ወይም በመኖሪያ አካባቢው ለሚገኘው የፓርቲው ህዋስ ማመልከት ይኖርበታል።**

**መስፈርቱን አሟልቶ የተመለመለ ግለሰብ ለ6 ወራት በሙከራ አባልነት ይቆያል**

## የቀጠለ…

- ሕዋስ የአንድ እጩ አባል አፈጻጸምን አይቶ ሙሉ አባል የማድረግ ወይም ተጨማሪ ከ3 ወራት ላልበለጠ ጊዜ የዕጩነት ቆይታ እንዲራዘም
- የዕጩ አባልነት ቆይታ ከአንድ ጊዜ በላይ አይራዘምም፤ ከክትትል ሂደትም ይሰረዛል
- ዕጩ አባሉ በሙከራ ጊዜ ቆይታው ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ ይፈጽማል

# አንቀጽ ዐሥራ አንድ - የአባል መብት

## ማንኛውም የፓርቲ ሙሉ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

- ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ፤
- በፓርቲው ጉባኤዎች የመሳተፍ፣ በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምፅ የመስጠት፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሕጋዊ መድረኮች ሐሳቡን በጽሑፍም ሆነ በቃል የማቅረብ፤
- በማንኛውንም የፓርቲ አካል ወይም አባላት በመረጃ የተደገፈ ገንቢ ሂስ የማቅረብ፤

## የቀጠለ…

- የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሮግራም፣ አቋሞችና ውሳኔዎች ለሌሎች የማሳወቅ፤ የማስተዋወቅ፤ የማሥረጽና በተጨባጭ እንዲተገበር የማድረግ

- በጽሑፍ አመልክቶ እና በእጆቹ የሚገኙ የፓርቲው ንብረቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አግባብ አስረክቦ ከአባልነት መልቀቅ ይችላል

## አንቀጽ ዐሥራ ሁለት - የአባልነት ግዴታ

- የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶችን የማወቅ፣ የመቀበል፣ የማክበር፣ የመገዛት እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል፤
- የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ የፓርቲውን የፖለቲካ ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ፤
- የፓርቲውን መርሆዎች፣ ዕሴቶችና የአባላትን የሥነ-ምግባር ሕጎችን የማክበር እና የፓርቲውን፣ የህዝብና የሀገርን ደኅንነትና ሉዓላዊነት የመጠበቅ፤

## የቀጠለ…

- የሀገሪቱን ሕጎች እና ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ውሳኔዎችን ማክበር፤
- የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፤
- በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የተያዙ ተናጠል ዕቋሞችን የፓርቲው በማስመሰል በማናቸውም መልኩ በሚዲያ ከማሠራጨት የመቆጠብ፤
- በአባላት መካከል የሚኖረውን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፍ ድርጊቶች የመታቀብ፤
- የአባልነት መዋጮ የመክፈል፤
- ከሙስና የጸዳ፣ ሙስናንና አድሎአዊ አሠራርን የመታገልና የማጋለጥ ግዴታ

## አንቀጽ ዐሥራ ሦስት - በአባላት ላይ በዲሲፕሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

በሚከተሉት ሁኔታዎች ከተግሣጽ ጀምሮ ከአባልነት እስከ ማሰናበት የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

- የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያላከበረ
- የአባልነት መዋጮ ለተከታታይ ለ6 ወራት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ካልከፈለ እና ውዝፍ መዋጮውን ለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ከአባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ይቆጠራል፤
- ማንኛውም አመራር ወይም አባል የሐሰት ሪፖርት መስጠትም ሆነ መጠቀም
- በፓርቲው ውስጥ አንጃነት እና ቡድንተኝነት መፍጠር ወይም ማስፋፋት

## የቀጠለ...

- ማንኛውም አባል የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆኑ ከተደረሰበት ከፓርቲ አባልነቱ ይሰረዛል፤

- በአገሪቱ ህጎች ጥፋት ተብለው የተቆጠሩ ድርጊቶችን ፈፅሞ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ በፓርቲው አሠራርም ተጠያቂ ይሆናል፤

## አባላትና ዕጩ አባላት የሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ክብደት እየታየ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡-

### ለሙሉ አባል፤

ሀ) ተግሣጽ፤

ለ) የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ሐ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

መ) ከኃላፊነት ማገድ፤

ሠ) ከኃላፊነት ዝቅ ማድረግ፤

ረ) ከኃላፊነት ማንሣት፤

ሠ) ከአባልነት ማገድ፤

ሸ) ከአባልነት መሠረዝ።

### ለዕጩ አባል፤

ሀ) የዕጩ አባልነት ለአንድ የሙከራ ጊዜ ማራዘም፤

ለ) ከዕጩ አባልነት መሰረዝ።

# ምእራፍ ሦስት

## አንቀጽ ዐሥራ አራት - የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት

**የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሀገሪቱን ሕገ መንግሥታዊ ፌዴራላዊ አወቃቀር የተከተለ ነው።**

ሀ) ፌዴራል፤

ለ) ክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፤

ሐ) ዞን/ከተማ/ክፍለ ከተማ/ልዩ ወረዳ/ቀበሌ፤

መ) ወረዳ//ከተማ/ክፍለ ከተማ፤

ሠ) ቀበሌ ናቸው

## ፓርቲው የሚከተሉት ተቋማዊ መዋቅሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) ጉባኤ፤

ለ) ማዕከላዊ ኮሚቴ፤

ሐ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤

መ) የፌዴራልና የክልል የፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ፤

ሠ) ፕሬዝዳንት፤

ረ) ምክትል ፕሬዝዳንቶች፤

ሰ) የኢንስፔክሽና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን፤

## የቀጠለ…

ሸ) የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት፤

ቀ) የፓርቲው የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች፤

በ) የብልጽግና የሴቶች ሊግ፤

ተ) የብልጽግና የወጣቶች ሊግ፤

ቸ) የፓርቲው መሰረታዊ ድርጅትና ህዋስ ናቸው።

የፓርቲው መሠረታዊ ድርጅትና ሕዋሳት አባላት በሥራ ቦታቸው በመኖሪያ አከባቢያቸው ይቋቋማሉ።

## አንቀጽ ዐሥራ አምስት - የፓርቲው ጉባኤ፣ የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር

- የፓርቲው ጉባኤ በፌዴራል ደረጃ እንደሚኖር
- በክልል ደረጃ ክልላዊ ኮንፈረንስ እንዲሁም በየደረጃው ከዞን እስከ ቀበሌ ኮንፈረንሶች እንደሚዋቀሩ
- በፌዴራል ተቋማት የሚገኙ የፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ እንደሚኖር የተመላከተበት ነው

## አንቀጽ ዐሥራ ስድስት - የፓርቲው ጉባኤ

- የፓርቲው ጉባኤ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው።

- የፓርቲው ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ዓመት ተኩል አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ የጉባኤው የመካሄጃ ጊዜ ከ3 ዓመት መብለጥ የለበትም።

- የጉባኤው ተሳታፊዎች ቁጥር ከ500 በላይ ሆኖ፤ ስብጥሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ

## አንቀጽ ዐሥራ ሰባት-የፓርቲው ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት፣

**ፓርቲው ጉባኤ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-**

➢የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል።

➢ፓርቲው የሚመራባቸውን አጠቃላይ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ያስቀምጣል፣

➢የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ቁጥር ይወስናል፣

➢ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገውን የውሕደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳብ ያጸድቃል።

## አንቀጽ ዐሥራ ስምንት - የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ፣

- የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤ ሆኖ ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ አካል ነው።
- ማዕከላዊ ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዝዳንት እና በምክትል ፕሬዝዳንቶቹ በጋራ ይመራል።

## ማዕከላዊ ኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነቶች ፡-

- የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ፣ የጉባኤው ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
- ፓርቲውን በበላይነት ይመራል፣ የፓርቲውን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አቅጣጫዎችና ዕቅዶችን እንዲሁም የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን ያመነጫል፣ አፈጻጸማቸውን በየጊዜው ይገመግማል።
- የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል።

## አንቀጽ ዐሥራ ዘጠኝ- የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤-

- ኮሚቴው በፓርቲው ፕሬዝዳንት ይመራል።
- መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል።

## አንቀጽ ሃያ አንድ-የፓርቲው ፕሬዝዳንት ተግባራትና ኃላፊነቶች

- የማዕከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፤
- ፓርቲውን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤ ስምምነቶችን ይፈርማል።

# አንቀጽ ሃያ ሁለት - የፓርቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች

- ፓርቲው 2 ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይኖሩታል፡፡

- ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ ተጠሪነታቸው ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ፤ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

- ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ በፕሬዝዳንቱ የተወከለው ምክትል ፕሬዝደንት ተክቶ ይሠራል፣

## አንቀጽ ሃያ አራት - የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት

- የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች ይኖሩታል፣
- ዕጩ የክልል/ከተማ አስተዳዳር የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን ከየክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የፓርቲ አመራሮች ጋር በመሆን ይለያል
- የዋናው ጽሕፈት ቤትንና የየደረጃውን የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶችን ዝርዝር አሠራርን አስመልክቶ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ረቂቅ መመሪያ ያቀርባል፤
- ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል።

# ምእራፍ አራት

## አንቀጽ ሃያ ስድስት- የክልል፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና የፌዴራል ተቋማት ፓርቲ ኮንፈረንስ የአሠራር ሥርዓት፣

- የክልል /አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ እና የፌዴራል ተቋማት የአባላት ኮንፈረንስ በዓመት አንድ ጊዜ፤
- የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳና የከተማ ኮንፈረንሳቸውን በዓመት ሁለት ጊዜ፤
- የቀበሌ፣ በየሦስት ወሩ ኮንፈረንሶች ይካሄዳሉ፣

## አንቀጽ ሃያ ሰባት - የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት

- በየደረጃው የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን
- የፓርቲው አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶች በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣
- የአባላቱን የፖለቲካ ብቃት እንዲዳብር ያደርጋል፣

## አንቀጽ ሠላሳ - የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ

- የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት
- የሴቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።
- ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሠራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሠራር መመሪያዎች ይኖረዋል።
- የብልጽግና የሴቶች ሊግ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።

## አንቀጽ ሠላሳ አንድ - የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ

- የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት

- የወጣቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።

- ዕድሜው ከ14-35 ዓመት የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አባል መሆን ይችላል

- ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የሊጉ አባል የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።

# ምእራፍ አምስት

## ❖ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ሠላሳ ሁለት - የሥልጣን ዘመን

➢የፓርቲው ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች የኃላፊነት ዘመን ጣራ 10 አመት ይሆናል፣

➢የሌሎች አመራሮች የኃላፊነት ዘመን ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

➢የአመራሮች የእድሜ ጣሪያ 65 ዓመት ይሆናል።

# አንቀጽ ሠላሳ ሦስት - የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች

1. ከአባላት መዋጮ፣
2. በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ከፓርቲው ደጋፊዎችና
3. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ይሆናል።

# የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፣

# ተልዕኮና አሰራር መመሪያ

# አንቀጽ 63. የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት

- የመሰረታዊ ድርጅት በክልል፣ በዞን፣ ከተማ፣ ወረዳና በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ሙሉና እጩ አባላትን ያካተቱ ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ህዋሳትን በመያዝ የሚደራጁ ናቸው

- የመንግስት ሰራተኞች /ለክልል፣ ዞን/ልዩ ወረዳ፣ ከተማ፣ ወረዳና ቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ላለ ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ፓርቲ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

- በየክልሉ ያሉ የፌደራል አባላት በሚሰሩበት ተቋም የሚደራጁ ሆኖ፤ ተጠሪነታቸው ለከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## የቀጠለ…

- የመምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች መሰረታዊ ድርጅት በተቋም ወይም በወረዳ፣ በቀበሌ የሚደራጅ ሆኖ ተጠሪነቱ ቀበሌ ወይም ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

- በሆስፒታል የሚሰሩ አባላት መሰረታዊ ድርጅት በተቋማቸው የሚቋቋም ሆኖ ተጠሪነቱ ለከተማ/ ለክ/ከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

- የከተማ ነዋሪዎች መሰረታዊ ድርጅቶች በመኖሪያ በቀበሌ/ወረዳ የሚደራጁ ሲሆን፣ ተጠሪነታቸውም ለቀበሌው/ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## የቀጠለ…

- በአንድ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም አንድ አካባቢ ተደራጅተው የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቁጥራቸው በቂ ከሆነ በአንድ መሰረታዊ ድርጅት ታቅፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

- ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው በክላስተር ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለየቀበሌያቸው ወይም ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል።

- በየትኛውም ደረጃ የሚቋቋሙ መሰረታዊ ድርጅት፣

ከ22 - 210 አባላት ይኖሩታል

10-12 አባላት ባሉት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ይመራል

አመራሩም በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ይመረጣል

- የአባላት ቁጥር ባነሰባቸው ቁጥራቸው እስከሚጨምር ድረስ ተመሳሳይ ባህሪና የቦታ ቅርበት ያላቸው በአንድ መሰረታዊ ድርጅት መደራጀት ይችላሉ

## የሚመረጡት የአመራር አባላት የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው

- በተሰማራበት የስራ መስክ ባስመዘገበው የስራ ውጤት ለሌሎች አርአያ የሆነ፣
- በሙያውና በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነና የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት የሚወጣ፣
- ለውጡን ወደፊት ይዞ የመሄድ ራዕይ ያለው አባል ይሆናል፣
- የፓርቲውን አሰራሮች በማወቅና ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርግ፣

## የቀጠለ…

- በተሰማራበት ስራ ሳይወሰን ከዚያ ውጭ በሚደረጉ ሌሎች የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከተ፣
- በአካባቢው ሕ/ሰብና የስራ ጓደኞቹ ዘንድ በስራውና በማሕበራዊ ግንኙነቱ የተሻለ ተቀባይነት ያተረፈ፣
- የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር አባላት ከልዩ ልዩ ህዋሳት አባላት መካከል እንዲመረጡ ይደረጋል

## የቀጠለ…

- የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር ኮሚቴ የራሱ
    1. ሰብሳቢ፣
    2. ምክትል ሰብሳቢ፣
    3. ፀሀፊንና
    4. ገንዘብ ያዥ ይመረጣል

- በስሩም ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል
    1. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ
    2. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ
    3. የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

## አንቀፅ 64. የመሰረታዊ ድርጅት ተልእኮ፡-

- በሚኖሩበት አካባቢ የሚካሄዱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጉዳዮች፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ተግባራት በብቃት እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት

- የአባላትና የአመራር አካላት ፖለቲካዊና ስነ-ምግባራዊ ብቃት ማጎልበቻ፣ የተሞክሮ መለዋወጫ መድረክ ሆኖ ማገልገል

- በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ አባል በተሟላ መልኩ ማስፋፋት

- በማያቋርጥ አኳኋን የአዳዲስ አባላት ምልመላ እንዲካሄድ ተገቢውን አመራርና ድጋፍ ይሰጣል፣

# አንቀፅ 65. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

- በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የፀደቀውን ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም በማዘጋጀት ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
- በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ አባልና መዋቅራቸው የማስፋት ስራ መከናወኑ ይረጋግጣል፣
- የህዋስ አመራርን ፖለቲካዊና የአመራር አቅም በሴሚናሮችና በግምገማ ነክ ስልጠናዎች በቀጣይነት የመገንባት ስራ ይሰራል፣

## የቀጠለ...

- የንዑሳን ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
- የህዋሳት ውይይት አፈፃፀምን ይከታተላል
- ፈጣንና ውጤታማ የግብረ መልስ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
- በስሩ የተደራጁ ህዋሳት ጠንካራ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል
- ከህዋሳት የሚቀርብለትን የእጩ አባላት ሪፖርት መሰረት በማድረግ ሙሉ አባል መሆን የሚገባቸውን ያፀድቃል

## የቀጠለ…

- በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ መሰረት ለመሰረታዊ ድርጅት የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፤

- መተዳደርያ ደንቡ መሰረት የአባላትን ቅጣት ይወስናል፡

- ለመሰረታዊ ድርጅቱ ኮንፈረንስ በየሦስት ወሩ፣
- አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ በየወሩ የተከናወነውን ፖለቲካዊና አደረጃጀት እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል

## የቀጠለ...

- የአባላትን ማህደር በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል

- ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶን ያከናውናል
- 
- የአባላት መዋጮ በደረሰኝ ሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ያደርጋል፡፡

- በአጠቃላይ አባላት ተልእኮአቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣

- ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስና በየደረጃው ላለው ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 66. የመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

- የመሰረታዊ ድርጅቱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
- የህዋስ አመራር ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ ስራን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል፡
- የጥናት ህዋሳት ጠንካራ የተደራጁ አሀዶች ሆነው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል
- የአመራር ኮሚቴውንና የመሰረታዊ ድርጅቱን ኮንፈረንስና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል

## የቀጠለ…

- ለስብሰባዎቹ የሚሆን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ወዘተ… ያዘጋጃል ወይም የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለስብሰባው ያቀርባል
- ከበላይ አካል ጋር ኮሚቴውን በመወከል ይገናኛል፡፡ ለበላይ አካል ሪፖርት ያቀርባል። ከበላይ አካል መመሪያ ይቀበላል
- ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴና ለየመዋቅራቸው ለፓርቲ ጽ/ቤ ኃላፊን ለኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 67. ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

- ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
- የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፡፡
- ከሰብሳቢው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
- ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና ለፖለቲካ ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 68. የፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

- ለአደረጃጀት ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ኮሚቴውን ያስተባብራል፡፡
- የመሰረታዊ ድርጅቱና የአመራር ኮሚቴዎችን ሰነድ ይይዛል፡፡
- ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
- ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና አደረጃጀት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 69. የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት

- ንኡስ ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነርሱም
    1. የመሰረታዊ ድርጅቱ ምክትል ሰብሳቢ ................ ሰብሳቢ
    2. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል . ም/ሰብሳቢ
    3. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ... አባል ይሆናሉ፡፡
- በዚህ ንኡስ ኮሚቴ ውስጥ
- የአባላት ፖለቲካዊ የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራ፣
- የስልጠና ኮንፈረንስ፣
- የአባላት ዓቅም ግንባታ ስራ፣
- በልሳናትና በብልፅግና መፅሔት ላይ የሚደረግ ውይይት ይደረጋሉ

# አንቀጽ 72. የአደረጃጀት ስራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሰራር

- ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነሱም፡-
    1. የመሰረታዊ ድርጅቱ ፀሀፊ ................................. ሰብሳቢ
    2. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .... ምክትል ሰብሳቢ
    3. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ...... አባል ይሆናሉ

## የንኡስ ኮሚቴው

- መረጃዎችና የአባላትን የግል ማህደር መያዝ፣
- የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎችን ተፈፃሚነት መከታተልና
- እያንዳንዱ አባል በአደረጃጀት ታቅፎ ተልዕኮዎቹን እየፈፀመ መሆኑን ይከታተላል
- አዳዲስ የአፈፃፀም ልምዶችን መቀመርና ወደ ሌሎች የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡

# አንቀጽ 74. የፓርቲው ፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

- የንኡስ ኮሚቴው አባላት ቁጥር ሁለት ሆኖ
    1. ሰብሳቢ
    2. ምክትል ሰብሳቢ
- በፓርቲው የገቢ እቅድ ማዘጋጀት፣ ገቢ ማሰባሰብና ማስገባት ዙሪያ የስራ ክፍፍል ይኖራቸዋል፡፡
- የፓርቲውን አመታዊ ገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት እና በእቅዱ መሰረት ማሰባሰብ፣
- ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ በመሰብሰብ ለፓርቲ ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋል፣
- የልሳናትና የብልፅግና መፅሔት የመፅሄት ሽያጭ ገቢ ያደርጋል፣
- ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 75. የመሰረታዊ ድርጅት አሰራር

- የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

- የኮንፈረንስ ጊዜ ቢያንስ ከ1 ወር በፊት አስቀድሞ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡

- የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ይሆናል፣

- የኮንፈረንስ አጀንዳዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ተመካክሮ ለጥናት ህዋሳት ማሳወቅና ጥናት ህዋሳት የሚፈልጉት አጀንዳ ካለ እንዲያካትቱ ማድረግ ይኖርበታል፣

- ልዩ ልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች የስራ አፈፃፀማቸውን በተመለከተ የየራሳቸውን ሪፖርት በአጭሩ እንዲያዘጋጁና በሪፖርቱ የቀጣይ እቅድም መነሻዎች እንዲቀርቡ ያደረጋል።

- ከበላይ አካል በኮንፈረንሱ ላይ ቢታዩ ይጠቅማሉ የሚባሉ አጀንዳዎችን በመቀበል ከየመዋቅራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለውይይት እንዲቀርቡ ይደረጋል፣

## የቀጠለ…

- በኮንፈረንስ መድረክ ላይ አጀንዳዎችን በማፅደቅ በቅደም ተከተል ውይይት ይደረግባቸዋል፣

- አባላት በየርዕሱ ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲቃወሙም ሆነ እንዲደግፉ ሰፊ እድል መስጠትና በበቂ ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ ወደ ውሳኔ ሃሳብ የማምራት አግባብን መከተል ይገባል፣

- የውሳኔ ሃሳቡ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ በንባብ እንዲቀርብና በድምፅ እንዲወሰን ይደረጋል፣

- በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የጋራ የአቋም መግለጫ ማውጣት፣ የአቋም መግለጫው ሁሉንም የውሳኔ ሃሳቦች በአጭሩ እንዲይዝ በማድረግ ለጥናት ህዋሳት ሃላፊዎች ኮፒ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል፣

## የቀጠለ…

- በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የአመራሩ ሂስና ግለሂስ ሪፖርት ለአባሉ እንዲቀርብ ማድረግ
- የአመራር ምርጫ በየአመቱ መጀመሪያ በሚካሄደው ኮንፈረንስ ይሆናል፣
- አባላት ወይም የበላይ አካል አስቸኳይ ኮንፈረንስ ሲጠይቁ ለመላ አባላት በጥናት ህዋሳት ስብስባ ላይ አሳውቆ ግማሽ ያህሉ ከደገፈው እንዲካሄድ ይደረጋል፣
- የኮንፈረንሱ አጠቃላይ ሂደት በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ይደረገል፣

# አንቀጽ 78. የመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አሰራር

**የአመራር ኮሚቴ ስብሰባና ግንኙነት**

1. አመራር ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡

በዚህ መሰረት፡-

- ከህዋስና ከንዑሳን ኮሚቴ የመጣለትን ሪፖርት፣ እንዲሁም ከበላይ አካል የሚወርድለትን እቅድና አቅጣጫ ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ለህዋሳትና ለንዑሳን ኮሚቴ አቅጣጫ ይሰጣል፣
- እጩ አባላትን ወደ ሙሉ አባልነት የማሸጋገር ውሳኔን ይወስናል፣ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለህዋስ ያሳውቃል፣
- አመራር ኮሚቴው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ያለውን ሃሳብ ለህዋሳት በአፋጣኝ ያሳውቃል፣

## አንቀጽ 80. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ከፓርቲ ጽ/ቤት ኮሚቴ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

- ሰብሳቢው ከፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር እና ከኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣

- የፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ኮሚቴ አመራሩ በ3 ወር አንድ ጊዜ የመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የፋይናንስ ሀላፊ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን አንድ ላይ ወደ ማእከል በመጥራት የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡

- እንደየአስፈላጊነቱ በየደረጃው ያሉት የፓርቲ ጽ/ቤት ፖለቲካና አደረጃጀት ኃላፊዎች ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር አባላት ጋር መደበኛ የስራ ግዚያቸውን በማይጋፋና ለነሱ አመቺ በሆነ ጊዜ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፣

## የቀጠለ…

- ከበላይ አካል የሚሰጠውን እቅድና ልዩ ልዩ መመሪያ ቆጥሮ ይቀበላል፡፡ እቅዶችን ለተፈፃሚነት ያዘጋጃል፣
- ለበላይ አመራር የሚቀርብ ትችት ካለው በዚህ መድረክ በመጠቀም ያቀርባል፣
- በየሶስት ወሩ የተሟላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ ይልካል፣

# አንቀጽ 81. የህዋሳት አደረጃጀት

- የህዋስ አባላት ቁጥር ከ11-35 ይሆናል፣
    1. በ4አመራር ኮሚቴ ይመራል

- ህዋሳት የሚመሰረቱት ሙሉና እጩ አባላትን በመያዝ
    1. በመኖሪያ አካባቢ
    2. በስራ ቦታ ሆኖ በሚከተለው መልኩ ይሆናል

## የቀጠለ…

- የመንግስት ሰራተኞች /በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳ/ልዩ ወረዳና በቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ በተቋም ወይም በየዘርፉ ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ይደራጃሉ፣

- በየክልሉ ያሉ የፌደራል ተቋማት አባላት ህዋሳት በሚሰሩባቸው ተቋማት የሚደራጁ ይሆናል፣

- የመምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና የተማሪዎች ህዋስ አመቺ በሆነበት ቦታ /ተቋም፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ ደረጃ ይደራጃል፣

## የቀጠለ...

- የሆስፒታል አባላት እንደ አመቺነቱ በሚሰሩበት ተቋም፣ ወረዳ/ቀበሌ ደረጃ ይደራጃሉ፣

- የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች ህዋሳት መንደር/ቀጠናን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡

- በገጠር የተሰማሩ የመንግስት ሰራተኞች ህዋሳት የገጠር ባለሙያዎች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ የስራ ቦታ ወይም ቀበሌን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡

## የቀጠለ…

- እያንዳንዱ ህዋስ የራሱን አመራር ኮሚቴ ይመርጣል

  እነዚህም፡-

  1. ሰብሳቢ
  2. የፖለቲካ ኃላፊ
  3. የአደረጃጀት ኃላፊ
  4. ገንዘብ ያዥ ይሆናሉ

- ለህዋስ አመራርነት የሚመረጡ አባላት የሚያሟሉት መመዘኛ ከላይ ለመሰረታዊ ድርጅት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 82. የህዋስ ተልእኮ

- አባላት በቀበሌያቸው/በወረዳቸው በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ በሚካሄዱ ብልፅግናን የሚያረጋግጡና የሰላም ተግባራት ግንባር ቀደም ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት በዚህ ሂደትም አባላትን በተግባር እንዲገነባ ይደረጋል፣

- በህዋሱ ውስጥ የታቀፉትን አባላት በሙሉ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የግል እቅድ ማፅደቅ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍና ውጤቱን መገምገም፣
- የአባላትን የፖለቲካዊና ድርጅታዊ ብቃት እንዲኖራቸው ይሰራል፣
- አዳዲስ አባላት ምልመላ ማካሄድ፣ አባላት በተደራጀ ፓርቲ ህይወት እንዲኖራቸውና የተደራጀ ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

# አንቀጽ 83. የህዋስ አሰራር

**ህዋሶች የሚከተለው ውስጣዊ አሰራር ይኖረዋል፣**

- **በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣**
- **የፖለቲካ ውይይት እና እያንዳንዱ አባል ብልፅግናን በሚያረጋግጡ ዙሪያ በግንባር ቀደምነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የአባላትና ደጋፊዎች የጋራ አደረጃጀት፣ በአጠቃላይም የአባላት እንቅስቃሴ የሚገመገምበት ይሆናል፣**
- **በግምገማው ላይ በመመስረትም የመማማር ፕሮግራም እንዲካሄድ ይደረጋል፣**
- **የህዋስ ስብሰባ የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣**
- **ማንኛውም አባል በህዋስ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት፣ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ምክንያት የማይገኝ አባል አስቀድሞ የህዋሱን ሰብሳቢ ማሳወቅና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡**

# አንቀጽ 84. የህዋሳት እንዲሁም የአመራር ኮሚቴና አባላት ተግባርና ኃላፊነት

**የህዋስ አመራር ኮሚቴ ተግባራት**

- የህዋሱን ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች ይመርጣል፣
- የህዋስ አባላት በተግባርና በአስተሳሰብ ግንባር ቀደም ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ይከታተላል፣
- ከመሰረታዊ ድርጅት የመጡ መመሪያዎችን የህዋሱ አባላት እንዲያውቋቸውና በአግባቡ እንዲፈፅሟቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፣
- አባላት ተልእኮቻቸውን ከመፈፀም አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ እያንዳንዱን አባል ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣

## የቀጠለ…

- አዳዲስ እጩ አባላት መስፈርቱን አሟልተው መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣ እጩ አባልነትን እንዲፀድቅ የውሳኔ ሀሳብ ለመሰረታዊ ድርጅት ያቀርባል፣
- የህዋሱን የውይይትና የግምገማ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በህዋሱ በማፅደቅም ስራ ላይ ይውላል፣
- የእጩ አባልነት ጊዜያቸው የሞላ አባላትን ሁኔታ ገምግሞ ወደ ሙሉ አባልነት ሊሸጋገሩ ይገባል ብሎ ያመነባቸውን ሙሉ አባልነታቸው እንዲፀድቅላቸው ለመሰረታዊ ድርጅት ሪፖርት ያቀርባል፣

## የቀጠለ…

- የህዋሱ የውይይት ፕሮግራም ሳይስተጓጎል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የሌሎችን ህዋሳት መልካም ተሞክሮ በመቅሰም ህዋሱ እንዲጠቀምበት ያደርጋል፣

- አመራር ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ መረጃዎችን ይለዋወጣል፣

- ለመሰረታዊ ድርጅት በየወሩ ሪፖርት ይልካል፣

## የህዋስ ሰብሳቢ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት

- የህዋሱን ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል፣
- የህዋሱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ በበላይነት ያስተባብራል፣
- ህዋሱን በመወከል ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር ይገናኛል፣
- ህዋሱ ጠንካራ የተደራጀ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣
- እያንዳንዱን የህዋስ አባል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፣

## የህዋስ ፖለቲካ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

- የአባላትን ፖለቲካዊ ዝንባሌ ተከታትሎ በማወቅ ሪፖርት በመደረግ
- ወቅታዊ ፖለቲካዊ የመወያያ ሰነዶች ላይ ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል
- የአባላት ፖለቲካዊ ግንዛቤ እንዲጎለብት ይሰራል

## የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

- ህዋሷ ጠንካራ ሆና እንድትንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣
- እያንዳዱ አባል በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ማጎልበትና በስራ ላይ እንዲያውል ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
- የህዋሱን አባላት ማህደር ይይዛል፣ ሲያስፈልግም ለመሰረታዊ ድርጅቱ ያስተላልፋል፣
- የአባላት የመማማር ሂደት ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ የየወቅቱን በእያንዳንዱ አባል ማህደር ያሰፍራል፣

## የቀጠለ…

- ህዋሱ እጩ አባል እንዲሆኑ የተቀበላቸውን አባላት ግንባታ ይከታተላል፣ ሙሉ አባል መሆን የሚገባቸውን በወቅቱ በህዋሱ እንዲገመገሙና ሪፖርቱ ለመሰረታዊ ድርጅት እንዲላክ ያደርጋል፡፡ ከመሰረታዊ ድርጅቱ የመጣውንም ምላሽ ህዋሱ እንዲያውቀው ያደርጋል፣

- የህዋሱ አባላት በአባላትና በደጋፊ የጋራ አደረጃጀት አማካኝነት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣
- ለመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት ኃላፊ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፣
- ተጠሪነቱ ለህዋሱ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅቱ የአደረጃጀት ኃላፊ ይሆናል፡፡

# የህዋስ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

- የአባላትን መዋጮ ያቅዳል፣ በህጋዊ ደረሰኝ በማሰባሰብ ለመሰረታዊ ድርጅት ገቢ ያደርጋል፣
- የልሳናትና የብልፅግና መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ገቢ ያደርጋል፣
- ሌሎች የፓርቲ ደጋፊ ገቢዎችን እንደአስፈላጊነቱ አሰባስቦ ገቢ ያደርጋል፣
- ተጠሪነቱ ለህዋስ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅት ፋይናንስ ኃላፊ ይሆናል፣


አመሰግናለሁ!